**<u>ማን፡እንደአንቺ፡</u>**

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ፈጥኖ፡ደራሽ፤

ሰላማዊት፡ልብን፡አዳሽ፤

አረጋጊ፡ እንባን፡አባሽ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡አዛኝቱ፤

የአምላክ፡እናት፡ድንግሊቱ፤

አማላጅ፡ነሽ፡የፍጥረቱ፤

ሰውን፡መላሽ፡ከስህተቱ።

ማን፡እንደ፡ አንቺ፡የሚያፅናና፤

የሚያወጣ፡ከፈተና፤

ደግፎ፡አቅፎ፡የሚያቀና።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ፀሎት፡ሰሚ፤

ጤና፡ላጡት፡አስታማሚ፤

አቤት፡ባይ፡ነሽ፡ሳታቅማሚ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡አስታራቂ፤

ሀጢአተኛን፡የማትንቂ፤

ጆሮ፡ዳባን፡የማታውቂ፤

መልካም፡ስራሽ፡አስደናቂ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡መከለያ፤

ታማኝ፡እናት፡መጠለያ፤

ቀና፡መንገድ፡መታመኛ፤

የንስሀ፡በር፡መግቢያ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ተቆርቋሪ፤

የማታልፊ፡የሰው፡ጥሪ፤

አቤት፡ብለሽ፡አናጋሪ፤

ሰማያዊት፡የኛ፡አብሳሪ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ለወደቁ፤

አዛኝ፡አፅናኝ፡ንፁህ፡እንቁ፤

ሰው፡ረስቶአቸው፡ለተናቁ፤

በሐዘን፡መከራ፡ለደቀቁ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡የሚራዳ፡

የምትሞይ፡የሁሉን፡ጓዳ፤

እባክሽ፡አውጪን፡ከአለም፡ፍዳ፤

ሁዋላ፡ጠፍተን፡እንዳንጎዳ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ምልእተ፡ፀጋ፣

ፀበልሽ፡ፈዋሽ፡ያለዋጋ፣

ለእኛ፡እኮ፡ነሽ፡ባለ፡አደራ፣

እባክሽ፡አውጪን፡ከሐጢአት፡ተራ፣

እንድንኖር፡ከአንቺ፡ጋራ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ያለው፡ለዛ፣

ንግግርን፡የሚያዋዛ፣

አንደበቱን፡እየገዛ፣

በረከትን፡የሚያበዛ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ልዩ፡ስጦታ፣

አምላክ፡ያደለን፡የነፍስ፡እርካታ፣

ደስ፡አለን፡ዛሬ፡ዲያብሎስ፡ሲመታ፣

መግቢያ፡መውጪያ፡አጥቶ፡ሲሄድ፡ባንዳፍታ፣

ስምሽ፡ግሩም፡ነው፡የህይወት፡ገበታ።

ማን፡እንደ፡አንቺ፡ታምረኛ፣

የኔ፡ላሉሽ፡ምስጢረኛ፣

አማላጅ፡ነሽ፡እውነተኛ፣

ዛሬም፡እባክሽ፡ነይ፡ወደኛ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ